የሚከብድ እና ቃላት የሌለው መሆኑን ነው። ማወቅ የፈለገ ሊኖረውና ሊታደመው ግድ ይላል። ያ ምሽት በአንድ ሰው ሕይወት ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ መለኪያ የለውም። የሌሊት ሶላትን (ቂያመ ለይልን) ስናዘወትር ሕይወታችን ይቀየራል። የሆነ ጊዜ የከበደን ሸክም ይቀልልናል። የማይፈቱ የሚመስሉ ችግሮቻችን ሁሉ ይፈታሉ። የሆነ ጊዜ ሩቅ መስሎ ይታየን የነበረው ወደ አምላካችን የመቅረብ ጉጉት የዕለት ተዕለት ሕይወታችን ይሆናል።

- 25 -

የጽልመቱ ሰዓት እና የሚመጣው ንጋት

"ከንጋት በፊት ያለው ጊዜ እጅግ የጨለመ ነው።" የሚል አንድ ቆንጆ አባባል አለ። እንደ የአስትሮኖሚ ተመራማሪዎች አባባል ደግሞ እጅግ ጽልመት የሚበዛው የሌሊቱ ከፍል ከዚያ በፊት ትንሽ ቀደም ብሎ የሚገኘው ነው። የዚህ አባባል እውነታ አጠቃላይ እና ዘይቤያዊ ነው። ያም ሆነ ይህ እውነታነቱ አናሳ ነው።

በሕይወታችን ውስጥ ብዙን ጊዜ እጅግ የጨለመ ጊዜ ያጋጥመናል። ብዙ ጊዜ እነዚያን የጭለማ ወቅቶች ተከትለው የሚመጡ ውጋጋን ግን እጅግ ምርጥ ናቸው። ሁሉ ነገር የተሰበረና ዋጋ የሌለው በሚመስልበት በዚያች ቅጽበት ያልተገመቱ ትናንሽ ነገሮች ይመጡና ከዚያ አጣብቂኝ ውስጥ ያወጡናል። ነቢዩላህ አዩብ (ዐ.ሰ.) አንድ በአንድ ሁሉን ነገር አጥተው ተስፋቸው ተሟጦ ነበር። ግና ከከባድ ትዕግስትና ምስጋና በኋላ መልሰው ሙሉ በሙሉ ተሠጣቸው። ሁሉ ነገር ተመለሰላቸው።

ለነቢዩ አዩብ ጨለማ ማለት ምንም ማለት አይደለም። እርሣቸው ጠንካራ አማኝ የአላህ ነቢይ ናቸውና። ለኛ ግን ዘላለም የማይገፈፍ የሚመስል ጽልመት ነው። ግና ይመስለናል እንጂ አላህ (ሱ.ወ.) የማያልቁ ምሽቶችን እንዳላደረገብን እንወቅ። እሱ አዛኝ የሆነ አምላክ ነው። በአዛኝነቱም ፀሐይን ሰጠን። እርግጥ ነው አንዳንድ ጊዜ ችግሮች ይከታተሉብንና መቼም የማያልቁ መስለው ይታዩናል። አንዳንድ ጊዜ ሙሉ በሙሉ ከአምላካችን ጋር የተቆራረጥን በሚመስለን መልኩ ኢማናችን ይወድቃል።የዚያ ዓይነቱ ሁኔታ ሲገጥመን ምንም በማናይበት ጨለማ ውስጥ የወደቅን ሁሉ ይመስለናል።

ግና ጨለማው ሲያበቃ ፀሐይ እንደምትወጣው ሁሉ የኛም ንጋት ይመጣል። በርሱ ወደር የለሽ እዝነት የተነሳ ነው ጽልመታችንን ይገፍልን ዘንድ የረመዷንን ብርሃን የሚልክልን። አላህ ረመዷንን የቁርአን ወርም አድርጎ ላከልን። ከሱ ተነጥለንና ርቀን እንዳንጠፋና ወደራሱም ሊያቀርበንና ከፍ ሊያደርገን። የተባረከውን የረመዷን ወር የሰጠን ባዶነታችንን እንድንሞላበት፣ ብቸኝነታችንን እንድንፈውስበት እና የነፍሣችንን ድህነት እንድናበለጽግበት ነው። ከጨለማ የምንወጣበትን የንጋት ብርሃን ላከልን። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡-

﴿ هُوَ ٱلَّذِى يُصَلِّى عَلَيْكُمْ وَمَلَٰٓئِكَتُهُۥ لِيُخْرِجَكُم مِّنَ ٱلظُّلُمَٰتِ إِلَى ٱلنُّورِ ۚ وَكَانَ بِٱلْمُؤْمِنِينَ رَحِيمًا ﴾

«እርሱ ያ በናንተ ላይ እዝነትን የሚያወርድ ነው፣ መላዕክቶቹም (እንደዚሁ ምህረትን የሚለምኑላችሁ ናቸው) ከጨለማዎች ወደብርሃን ያወጣችሁ ዘንድ (ያዝንላችኋል) ለአማኞችም በጣም አዛኝ ነው።» (አል-አሕዛብ : 43)

ይህ አዝነቱ አዝነቱን ለሚፈልጉ ሁሉ የሚዳረስ ነው። ሌላው ቀርቶ እጅግ ጥፋተኛና ኃጢአተኛ የሆነ ሰው እንኳን ተስፋ እንዳይቆርጥ ተጋብዟል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡-

﴿ قُلْ يَٰعِبَادِيَ ٱلَّذِينَ أَسْرَفُوا۟ عَلَىٰٓ أَنفُسِهِمْ لَا تَقْنَطُوا۟ مِن رَّحْمَةِ ٱللَّهِ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ يَغْفِرُ ٱلذُّنُوبَ جَمِيعًا ۚ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلْغَفُورُ ٱلرَّحِيمُ ﴾

«በላቸው፡- እናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ! ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ፣ አላህ ኃጢአቶችን በመላ ይምራልና። እነሆ እርሱ መሓሪው፣ አዛኝ ነውና።» (አዝ-ዙመር : 53)

አላህ (ሱ.ወ.) አዛኝ እና ሩህሩህ ነው። የታላቅ እዝነት ባለቤትም ነው። ረመዷን ከየትኛውም ጊዜ በላይ የአላህ እዝነትና ምህረት የሚወርድበት ወር ነው። አላህም በውስጡ ለምእመናኑ በእጅጉ ያዝናል። የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ይህንኑ አስመልክተው

"የመጀመርያ ክፍሉ እዝነት፣ መካከሉ ምህረት የሚታደልበት፣ የመጨረሻው ክፍሉ ከእሳት ነፃ የሚወጥጣበት ነው።" ብለዋል። (ኢብኑ ኹዘይመህ እንደዘገቡት)

እያንዳንዱ የረመዷን መምጣት ወደ አላህ (ሱ.ወ.) እንድንመለስ የሚጋብዘን ነው። ዛሬ ላይ ምንም እንሥራ ምን እያንዳንዱ ሁኔታችን የእጃችንና የሥራችን ውጤት ነው። መልካም ከሆነ መልካም፤ መጥፎ ከሆነ መጥፎ። እኛ ኃጢአቶቻችንን የምናምን እና ወደ አላህም የምንዋደቅ ከሆነ በርግጥም ማድረግ ያለብንን ነው ያደረግነው። ከወደቅንበትና ከተናነስንበት የሚያነሳንም አላህ (ሱ.ወ.) ብቻ ነው። በተከታታይ እና በቋሚነት ለሱብሒ ሶላት መነሳት የሚያቅተን ከሆነ ፤ ወይም ደግሞ ከሐራም ርቆ መቆየት የሚችግረን ዓይነት ሰው ከሆንን በዚህን ጊዜ ከአላህ ጋር ያለንን ግንኙነት ልንፈትሽ ይገባል። አብዛኞቻችን ራሳችንን እናታልላለን። ይህ መሆን የለበትም። በዚህ ምድር ላይ እየሆነ ያለው ነገር ሁሉ ስኬት ይሁን ውድቀት፣ የምናገኘውም የምናጣውም፣ የሠራነውም ያልሠራነውም በአላህ ፈቃድ እና ይሁንታ ብቻ እንደሆነ ልናውቅ ይገባል። ከአላህ እገዛ ውጭ በራሳችን ቅንጣት ታክል ተጽእኖ ኢይኖረንም። የምንወድቀውም ሆነ ስኬት የምናስመዘግበው ከፈጣሪችን ጋር እንዳለን ቅርበትና ርቀት ነው። ስለዚህ ከአላህ አንፃርም ሆነ ከሰው አንጻር ጥሩ ልንሆን ይገባል።

ግና አላህ (ሱ.ወ.) እንደሰው ልጅ አይደለም። ብናጠፋም ቂም አይቋጥርብንም። ያለፈ ጥፋታችንን ሰርዞ የሥራ ዝርዝራችን የሚሰፍርበት አዲስ እና ነጭ መዝገብ ይሠጠናል። ረመዷን የዚህ ዓይነት ዕድል አለው። የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) "ረመዷንን በሙሉ እምነትና ምንዳውን አላህ ዘንድ በመተሳሰብ የፆመ የቀደመ ወንጀሉ ይማርለታል።" ብለዋል።

ታዲያ የዚህ ዓይነት ዕድል ተሰጥቶን የቻልነውን ሁሉ መጠቀም ሲገባን ለምን ያቅተናል!? ሁለት መርሳት የሌለብን ነገሮች አሉ።

ለምን እንደምንፆም እንወቅ

ብዙ ሰዎች ዝም ብለው መንፈሳዊነቱን ብቻ አስበው ለመፆም ብቻ ነው የሚፆሙት። ትርጉሙን በትክክል ሳይገነዘቡ ነው የሚፆሙት። ሌሎች ደግሞ ድሆች ያሉበትን ሁኔታ ስለሚያስታውሰን ስሜታቸውን የምንጋራበት አጋጣሚ ነው ይላሉ። በርግጥ ይህ ፆም ሊኖረው የሚችለው ቆንጆ ውጤትና ፍሬ ነው። ግና ዋና ዓላማው አይደለም። ዋና ዓላማውን አላህ (ሱ.ወ.) በቁርአኑ ውስጥ ገልፆታል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُتِبَ عَلَيۡكُمُ ٱلصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ ﴾

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ፃም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ህዝቦች) ላይ እንደተጣፈ በናንተም ላይ ተጣፈ (ተደነገ)፣ ልትጠነቀቁ ይገባልና።»

(አል-በቀራህ : 183)

ሥጋዊ ፍላጎቶቻችንን በመያዝ እና በመቆጣጠር ታላቁን ጦርነት ማሸነፍ እንችላለን። ራሣችንን መቆጣጠርና ነፍሳችንን መግዛት ነው ትልቁ ጦርነት። ስንፆም እያንዳንዱ የርሃብ ስሜት ለሱ ብለን ይህን መስዋእት የምንከፍለውን አምላካችንን ያስታውሰናል። አላህን (ሱ.ወ.) በተከታታይነትና በዘላቂነት በማውሳት እና ለሱ ራሣችንን በማስገዛት የሱን ሕያውነት ከኛ ጋር መሆን ማረጋገጥ እንችላለን። በዚያ መልኩ ሲሆን ነው ለአላህ የሚኖረንን የአላህ ፍራቻ (ተቅዋ) ሊጨምር የሚችለው። ማንም ሰው በማያየን ሁኔታ ላይ እያለን መብላት ስንችል፤ እንዳንበላ የሚከለክለን ሁኔታና የውስጥ ስሜት ነው ተቅዋ ማለት። ያ ስሜት ሲድነና ጎልብቶ ሌሎች ወንጀሎችንም ከመሥራት ይከለክለናል። ይህ የረመዳን ሥልጠና ውጤት ነው።

ዖምህን ርሃብ እና ጥም ብቻ አታድርግ

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

"መጥፎ ንግግርን እና መጥፎ ድርጊቶችን ያልተወ ሰው ምግቡንና መጠጡን ቢተው አላህ ጉዳዩ አይደለም።" (ቡኻሪ እንደዘገቡት)

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ በማለትም አስጠንቅቀዋል ፡-

"ብዙ ሰዎች አሉ፤ ከጾማቸው ርሃብ እና ጥም ብቻ የሚተርፋቸው። ብዙ ሰዎች አሉ ሌሊት በመቆማቸው ድካም ብቻ የሚተርፋቸው።" (አድ-ዳሪሚይ እንደዘገቡት)

ስንፆም ሙሉ ስዕሉን ልናገኝ እና ልንገነዘብ ይገባል። ፆም ከምግብ ርቆ መቆየት ብቻ አይደለም። የተሻለ ሰው ለመሆን መጣር መታገል እንጂ።

በመጣር እና በመታገል ከአምላካችንን የተነጠልንበትን የጨለማ ኑሮ እንድንሻገር ዕድል ተሠጥቶናል። ግና ፀሐይ ጠዋት ላይ ወጥታ ማታ እንደምትገባው ሁሉ፤ ረመዷንም በልባችን ላይ ትዝታን ጥሎ ይሄዳል።

- 26 -

ስለ ሞት

ይህን ጽሑፍ የጻፍኩት አንድ መልካም ሰው ቀብረን በመመለስ ላይ እያለን መኪናዬ ውስጥ ሆኜ ነው። አላህ ይዘንለት። ለቤተሰቡቹም እንዲሁ።

ዛሬ አንድ ሰው ቀበርን። እሱን ከቀበርን በኋላ እኔ በሕይወት ካሉ ቅፍለቶች መካከል ተገኝቼ እዚህ ነው ያለሁት።

ለጊዜው እኔም ሆንኩ እናንተ በሕይወት ካሉት ውስጥ ነን። የተለየ ዓለም ስላለን አይደለም የቀረነው። እነሱ የሚሄዱ እኛ የምንቀር ስለሆን አይደለም አሁን ያለነው። ግና ለጊዜውም ቢሆን ቅፍለታችን ወደኋላ ስለቀረ ነው። ምናልባት አሁን እነርሱን ቀብረን ወደቤታችን እየተመለስን ሊሆን ይችላል። አልጋችን ላይ ቲቪ እያየን፣ ሥራችን ላይ፣ ፈተና ላይ፣ ከጓደኞቻችን ጋር፣ ፌስቡክ ላይ ተጥደን አሊያም ሌላ ቦታ እንሆን ይሆናል። ምናልባት አሁን እየተመለስን ያለነው ጊዜ ወደምናሳልፍባቸው ነገሮች፣ ወደ ጣአቶቻችን፣ ወደ ማታለያዎቻችን ሊሆን ይችላል። በርግጥም ይኸው ነው።

እኔ ግን እየነዳሁ ያለሁት ወደ አልጋዬ፣ ወደ ቲቪዬ፣ ወደ ሥራዬ፣ ወደ ፈተናዬ፣ ወደ ጓደኞቼ፣ ወደ ፌስቡኬ፣ ወደ ቻቴ አይደለም።

እየተመለስኩ ያለሁት ጊዜዬን ወደማሳልፍባቸው ወደነኛ ነገሮች፣ ወደ ጣአቶቼ፣ ወደ ማታለያዎቼ አይደለም።

እየነዳሁ ያለሁት ወደተነሳሁበት ነው። እየነዳሁ ያለሁት እሱ ወደሄደበት ተመሳሳይ ወደሆነ ቦታ ነው።

ወደዚያው እየነዳሁ ባለሁበት ሁኔታ ግን እዚያ ለመድረስ ምን ያህል ጊዜ እንደሚፈጅብኝ አላውቅም።

እየነዳሁ ያለሁት ወደተነሳሁበት ነው። ከአላህ ጋር። ምክንያቱም አላህ “አል-አወል”/ የመጀመርያ/ ነው። አላህ “አል-ኣኺር” /የመጨረሻ/ ነው።

አካሌ ወደዚያ እየወሰደኝ ነው። ግና ባዶውን ነው የሚንቀሳቀሰው። መንቀሳቀስ ብቻ። እዚያ ስደርስ እንደገና ወደኋላ ይቀራል። ልክ ዛሬ እንዳደረገው። አካል ከአፈር ነው የመጣው። ወደመጣበት ወደ አፈርም ይመለሳል። ገላ ቀፎ ብቻ ነው። የነፍስ መያዣ ቀፎ። ለጊዜው ወዳጄ ሊሆን ይችላል። ከኔ ጋር ሊቆይ ይችላል። ግና ቀኔ ሲደርስ ትቼው

እሄዳለሁ። ግና ለዘላለሙ አልለየውም። ምክንያቱም ቤቴ ያ እንጂ ይህ አይደለምና። ለዚህም ነው አላህ (ሱ.ወ.) መልካሟን ነፍስ ወደራሱ ሲጠራት-

﴿ ٱرۡجِعِيٓ إِلَىٰ رَبِّكِ ﴾ "ወደ ጌታሽ ተመለሺ" የሚላት።

ያች የቀበርናት ውብ እና ቆንጆ ምርጥ ነፍስ ከዛሬው ሕይወት አልተለየችም። ግና ወደ ከፍተኛው እና አላህ ወደመረጠላት ምርጥ የሆነው ቤት ነው የተሸጋገረችው። የሄደም ሰው ደግ ከሆነ ወደ ቤቱ ነው የሄደው። ወደ መልካም ቤቱ። ሰውነቱ የዚህ ዓለም ስሪት ነውና እዚህ ትቶት መሄዱ ግድ ነው። ሰውነት የዚህ የትንሹ ዓለም ባህሪ ነው። መብላት፣ መጠጣት፣ መድማት ማልቀስ ያለው እዚህ ነው። መሞትም ያለው እዚህ ነው። እነኚህ ሁሉ የዚህ ዓለም ባህርያት ናቸው። ነፍስ ግን የላዕላዩ ዓለም ስሪት ናት። ስለሆነም ዋንኛ ፍላጎቷ አንድ ነገር ብቻ ነው። ከአምላኳ ጋር መሆን።

ሰውነት በቁሳዊው ዓለም እጦት ምክንያት እንደሚያለቅሰው፣ እንደሚደማውና ህመም እንደሚሰማው ሁሉ፤ ነፍስ በነኚህ ነገሮች የምትነካ አትሆንም። ነፍስን ሊጎዳት አሊያም ሊረብሻት የሚችለው አንድ ነገር ብቻ ነው። የሚገድላት አንድ ነገር ብቻ ነው። እሱም የፈለገችውን ነገር ያጣች እንደሆነ ነው። እሱም ወደፈጠራት መነሻዋ አለመቅረቧ ነው። ወደ አምላኳ አለመጠጋቷ ነው። ስለሆነም ሕያው ለሆነች ነፍስ ላናለቅስ አይገባም። አልሞተችምና። ማልቀስ የሚገባን ሕያው ከሚያረጋት ከአምላኳ ርቃ ለሞተችው እና በአካል ብቻ ላለችው ነፍስ ነው። የሰውነት መኖር ትርጉም የለውምና።

ሌላው ቀርቶ በዚህ ምድር ላይ የአማኝ ነፍስ ወደቤቷ ትሮጣለች።

አምላኬ ሆይ! ነፍሴን በተቀደሰችና ጥብቅ በሆነች ቦታ አስቀምጣት። ማንም ሊረብሻት በማይችል ቦታ አስቀምጣት። ፀጥታ እና ሰላም በሰፈነበት ቦታ። በውጫዊው ዓለም በማትረበሽበት ቦታ። አላህ በቁርኣኑ "የረካሽ ነፍስ" ብሎ እንደጠራት ነፍስ፡-

አላህ ሱ.ወ. በቁርአኑ -

﴿ ٱرۡجِعِيٓ إِلَىٰ رَبِّكِ رَاضِيَةٗ مَّرۡضِيَّةٗ ٢٨ فَٱدۡخُلِي فِي عِبَٰدِي ٢٩ وَٱدۡخُلِي جَنَّتِي ﴾

«(ስአመነች ነፍስም) አንቺ የረካሺው ነፍስ ሆይ! ወዳጅ ተወዳጅ፤ ኾነሽ ወደ ጌታሽ ተመለሽ። በባሮቼም ውስጥ ግቢ፤ ገነቴንም ግቢ (ትባላለች)።»

(አል-ፈጅር : 27-30)

እንዳላት ነፍስ አድርጋት።